# የማያዛልቅ ፀሎት ለቅስፈት

ጉድ ይሰማ ጆሮ ነውና የሰላማዊ ትግል ሐዋርያ ነኝ ሲሉ የቆዩት ፕሮፌሰር ዛሬ ደግሞ ወደ ባዕድ ሀገር ተጉዘው ኢትዮጵያውያንን ተንስዑ ለፀሎት ማለቱን-- ፀልዩ--ማለቱን ተያይዘውታል። እግሩን መሬት ላይ የተከለው የድርጅታቸው ዋና ፀሀፊግን በባዕድ ሀገር ያሉትን ዜጎች ወደ አንድ ሚለዮን የሚጠጋ ዶላር ብትለግሱን በሰላማዊ ትግል መለስ ዜናዊን እንጥለዋለ ን ብሎ ቃል ገብቶ ተማፅኗል። ቀደም ሲል ከሚሊዮን ዶላር በላይ ተለግሶ ገንዘቡም ደብዛው አልተገኘ፤ መለስም ከቤተ መንግስት አልወጣ።

ይህ ሁሉ በደፈናው ፈገግ አስደርጎን ባለፈ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአብዛኛው አማኝ በመሆኑ ዛሬ እንደ አዲስ ያውም ከእኚህ ፕሮፌሰር ፀልዩ የሚል ምክርን ጠባቂ አይደለም ማለትም ይቻላል። ለነገሩ የማያዛልቅ ፀሎት ለቅስፈት የተባለውም እዚህ ቢነሳ ቦታው ነው። ፀልዩ፤ ብረት የሚያነሳን ገዝቻለሁ፤ በሰላም ብቻ ታገሉ ወዘተ የሚለው የተጠናከረ ሰበካና ቁጣ በመሰረቱ የወያኔን አገዛዝ እቀፉ ለመሆኑ ብዙ ክርክርን ጠያቂ አይደለም። በመጪ ው የወያኔ ምርጫ መሳተፍ እንደ ዋና አማራጭ እየተገፋ ነው በነዚህ ክፍሎች ወይም በመሳበሰብ ላይ ባሉ ቡድኖች። በ1997 ግንቦት ምርጫ አለምንም የምርጫ ህግና ኮሚሽን ለውጥ የተደረገው ተሳትፎ ያስከተለውን ጉዳት ገና ሳንረሳ በወያኔ ምርጫ እንሳተፍ ጥሪ አልፋ ኦሜጋው ለወያኔ እጅ መስጠትና ለአገዛዙ ዕድሜ መቀጠል መሆኑን እንፀልይ እንምረጥ-- ባዮቹ ሊሸፍኑት የሚች ሉት ሀቅ አይደለም። ያም ቢሆን የሰላም ትግል የተባለውን በተመለከተ ፕሮፌሰሩም ሆነ ሌሎች የሚሰብኩት ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ከተባለው ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ማየት ከባድ አልሆነም።

ሰላማዊ ትግል ማለት እጅ መስጠትና እሱ ያመጣውን እሱ እስኪመልሰው ብሎ አቀርቅሮ መገዛ ት ማለት አይደለም። ሰላማዊ ትግል ማለት ከገዢው ሀይል ጋር መደራደርና ለገዢው ቡድን ታዛዥና ተገዢ መሆን ማለት አይደለም። ሰላማዊ ትግል ዝምታ፤ በጫንቃ የተጠላውን ቀንበር መቻል፤ ጨዋ መሆን ማለትም በጨዋነት ለአረመኔ መገዛት ማለትም አይደል። ሰላማዊ ትግል ማለት በስልጣን ያለውን ሀይል መታገል ማለት ነው። ዛሬም ነገም ተነገ ወዲያም አገዛዙ እስኪወ ድቅ ድረስ መታገል። በምን መንገድ? በሰላማዊ ሰልፍ፤ በስራ ማቆም አድማ፤ በኤኮኖሚ ማዕቀብ ፤ ከአገዛዙ ጋር በምንም መስክ ባለመተባበር፤ በረሀብ አድማ፤ በሙት ከተማ አድማ፤ በአጠቃላይ ሀገር አቀፍ ስራ ማቆም አድማ ወዘተ መታገል ማለት ነው። እስቲ በዚህ ዓይነት ተቃውሞ ሲሳተፉ ወይም ሲመሩ የታዩ ፕሮፌሰሮች ይጠቀሱ ቢባል መልስ ይከብዳል። ፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ብለው ሻማ አብርተው አንዴም ሲቃወሙ ታይተዋል? ስንት የስራ ማቆም አድማ ተጠራ ?ተደረገ ? የሙት ከተማ አድማውን ዝግጅት ያከሸፉት የሰላማዊ ትግል አራማጆች ነን ሲሉ የነበ ሩት አልነበሩምን? በወያኔና አጋሮቹ ላይ የኤኮኖሚ ማዕቀብ እናድርግ ብሎስ ምን ያህል ቅስቀሳ ተካሄደ? ለወያኔ ግብርና ክፍያ አታድርጉ ጥሪስ ተሰማ? እንኳን ሸለላ ቅንቀናውም አልተሰማ ነው ነገሩ። ስለ ሰላማዊ ትግል የሚለፈፈው ሁሉ ሕዝብን ትጥቅ ለማስፈታት እንጂ እውነትም ይህን ዕልህ አስጨራሽ ትግል ለማካሄድ ታስቦ እንዳልሆነ ባለፈው 17 ዓመታት ለመታዘብ

ተገደናል።

ለዚህ ነው ይህ አዲስ ፀልዩ እንፀልይ ሰበካ አንድም ፖለቲካና ሀይማኖትን ማደባለቁ ብቻ ሳይሆን በይዘቱም ቅስፈት ሊያመጣብን ይችል ይሆናል የምንለው። ፀልዩ ከልብ ሳይሆን ፀልዩ አትታገሉ ነው መልዕክቱ። በ2002 የወያኔን አገዛዝ-- መለስ ቀጠለ አልቀጠለ --በምርጫ ቧልቱ ለማጀብ ከወዲሁ ዝግጅቶች እየተካሄዱ መሆናቸው ከሕዝብ የተደበቀ አይደለም። ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን በክፍፍልና በአንጃ እያዳከሙ፣ አዳዲስ ስብሰቦችን በምርጫ ተሳታፊነት ዙሪያ እያቋ ቋሙ እንዳሉ እያየን ነው። ይህ ሴራ እንዲሳካ ፀረ ወያኔ ትግል የሚያካሂዱ ድርጅቶች መዳከም አለባቸው። አንድም በውስጣቸው አንጃን በመቀስቀሰና በመከፋፈል በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝብ ከትግል እንዲርቅ አደናጋሪ ሰበካን በማካሄድ። በአደናጋሪ ሰበካ ደረጃ ወያኔን ጠላት አትበሉ፣ ትጥቅ ትግል ውጉዝ ከመ አርዮስ ይሁን፣ ፀልዩ እንፀልይ ወዘተ ሰበካዎች የሚጠቀሱ ናቸው። ተጨምቀው ሲታዩ መልዕክታቸው ሽንፈትና ቀቢፀ ተስፋ እንጂ ትግልና ቆራጥነት-አምቢተኝነት አይደለም። ሰላማዊ ትግል ግን የሚገለፀው በፅና እምቢተኛነት ነው። መስዋዕትንትን በድፍረት ከፍሎ ትግልን መቀጠል። ምህረት ጥየቃ ፅናትን ትግልን ሊተካ አይችልም፣ አይገባውም ማለት ነው። ሰለማዊ ትግል የፈሪ መደበቂያ ሳይሆን የጀግና መለያ መድረክ መሆኑን የእኛዎቹ ገና አልተረዱም ወይም ከልብ መቀበል አልቻሉም ማለት እንችላለን። ስለዚህም ስለ ሰላማዊ ትግል የተሳሳተ ግንዛቤን ሲያሰራጩ በሌላ በኩል ደግሞ ከወሬው በዛ ከትግሉ ጠፋ መፈክራቸው ሆኖ ለትዝብት ይዳርጋቸዋል።

በአማኞች ዘንድ ፀሎትም መሳሪያ ነው--ይህ የሚካድ አይደለም። በትግል ሜዳ ደግሞ ጠላትን ፊት ለፊት ገጥሞ መዋደቅ የግድ ነው።ሌላ አማራጭ የለውም። የቀበሮ ባህታውያን ሰበካ ነብር ፍየል ሆኗል ባይ ነውና ሰሚ ካገኘ ትግልን ያስተኛል፣ወያኔን ይጠቅማል። ተደጋግሞ እንደተገለፀ ወ በወያኔ አገዛዝ ስር ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ መቸም ቢሆን ሊካሄድ የሚችል አይደለም። ችግሩ ከመለስ ዜናዊ ሳይሆን ግለሰቡ መሪ ሆኖ ከተቀመጠበት አገዛዝ ወይም ስርዓት ነው። አገዛዙ ካል ተወገደ፣የወያኔ ባልስልጣንነተት ካባበቃ ለውጥ ሊኖር አይችልም። ወያኔን አጅበው ኢትዮጵያን የሚቦጭቁ ጉማጅ ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል እንጂ ከመለስ አገዛዝ ጋር በማበር ለሕዝብ የሚፈይ ድ ለውጥ ከቶም የሚገኝ አይሆንም። የሕዝብ ዝምታና በጨዋነት ተገዢነት የተፈለገው ወይም በሰላማዊ ትግል ሽፋን የወያኔን የበላይነት መቀበል የሚሰበከው ሊበሉ ለፈለጉ ሁኔታው ሳይረበሽ አመቺ እንዲሆንላቸው ብቻ ነው። ለዚህም ነው የሕዝብ መነሳሳትና ማመፅ ወያኔን ብቻ ሳይሆን እነሱንም የሚያስፈራቸው። በግንቦት 97 የሕዝብ ታሪካዊ ተቃውሞ እንቅስቃሴ "መስመር ይስታል፣ከቁጥጥ ር ይወጣል" ብለን ሰግተን ነበር ሲሉ መፅሀፋቸው ውስጥ ያሰፈሩት ወያኔዎች አልነበሩም።

ማዕቀብ ሲባል ማዕቀብ አይጠቅምም ቆራጥ ትግል እንጂ፣ ሁለገብ ትግል ሲባል የለም ሰላማዊ ትግል ብቻ፣ ማመፅ ሲባል የለም ፀልዩ መባሉ የሚያሳየው በዚህም ሆነ በዚያ ወያኔን ለመጣል አትታገሉ ነው። ያለውን አረመኔ አገዛዝ ጠላት አትበሉ፣ ጠላት የሚሉ ስልጡን ፖለቲካ ያልገባ ቸው ናቸው፣ የጥላቻ ፖለቲካ ያብቃ ሲሉ የሚደመጡት ሁሉ በቀጥታ ወያኔ ካልሆኑ በተዘዋዋሪ ግን የወያኔ ጀሌዎች መሆናቸው ግልፅ ነው። የፍቅርና የሰላም ሐዋርያዎች፣ ፀልዩ እንፀልይ ባይ ሰባኪዎች ሲበዙ መጠርጠር ሲያንስ ነው። በተለይ ሰባኪዎቹን የምናውቃቸው ከሆነማ መሰሪ ተልዕኮአቸው ሊደበቀብን አይችልም። መፀለዩን እንፀልይ ግን የወያኔን አገዛዝ ማለትም ጠላታች ንን በቆራጥ ትግል ከመጥበስና ማረኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሎ እንዲለምን ከማድረግ የሚያግደን ማንም ኃይል አይኖርም፣ እንዲኖርም አንፈቅድም።